# ስለ ወባ
# በሽታ በጥቂቱ

## የወባ በሽታ ምንድን ነው?

- የወባ በሽታ በወባ ትንኝ አማካኝነት ከወባ በሽተኛ ወደ ጤነኛው ሰው የሚተላለፍ ህመም ነው።
- የወባ ትንኝ የምትናደፈው አብዛኛውን ጊዜ በምሽትና በሌሊት ነው።
- የወባ ትንኝ በኩሬዎች፣ በረግረግ ቦታዎችና፣ በሌሎችም ውሃ በረጋባቸው ስፍራዎች ትራባለች።



## ወባን እንዴት እንከላከላለን?

በፀረ ወባ ትንኝ መድሃኒት የተረጨ አጎበር መጠቀም

መኖሪያ አካባቢያችን በፀረ ወባ ትንኝ መድሀኒት መርጨት

የወባ ትንኝ ወደ አጎበሩ ውስጥ እንዳትገባ አጎበሩን ከመኝታ ቦታ ጋር በትክክል ወጥሮ መያዝ

አጎበራችን እንዳይቀደድ ወይንም እንዳከቃጠል ጥንቃቄ ማድረግ፤ ተከቀደደም ወድያውኑ መስፋት ይኖርብናል።

# የወባ በሽታ
# ምልክቶች ምንድን ናቸው?

- ትኩሳት፣ ላብ ፣ ራስ ምታት ፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ምግብ ፍላጎት መቀነስ ናቸው።
- በወቅቱ ህክምና ካልተወሰደና በሽታው ከጠና ደግሞ ህሊናን መሳት፣ ቅዠትን፣ የጉበት በሽታን እና ሞትን ሊያስከትል ይችላል።
- እነዚህን ምልክቶች እርሰዎ ወይም ቤተሰብዎ ላይ ከታዩ በአስቸኳይ በአካባቢዎ ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ በመሄድ ህክምና ይከታተሉ።

ወባን እንከላከል !



በዓለም ላይ በየቀኑ ከ2,000 በላይ ህፃናት በወባ ትንኝ ይነደፋሉ

# ወባ ለሞት
# የሚዳርግ በሽታ ነው

EPaRDA TULLOW

## ስለ ወባ በሽታ በጥቂቱ

**የወባ በሽታ በወባ ትንኝ አማካኝነት ከወባ በሽተኛ ወደ ጤነኛው ሰው የሚተላለፍ ህመም ነው።**



ወባ በአብዛኛው ነፍሰጡር እናቶችና እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ሕፃናት ልጆችን ያጠቃል። ወባ በአስቸኳይ ህክምና እርዳታ ካልተገኘ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው።

ወባን ለከላከል ብዙ ወጪ የማይጠይቅ ነገር ነው።



**ወባን እንከላከል !**

## ምን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይገባናል?

- የፀረ ወባ ትንኝ መድሃኒት ሲረጭ ከምግብ፣ መጠጥ ውሃ፣ መመገቢያ እቃዎች ማራቅ ይገባናል።
- የወባ መድሃኒቶችን በጤና ባለሞያ በታዘዘውመሰረትበአግባቡ እና ሳያቋርጡ መውሰድ ይገባል።
- መድሃኒት መውሰድ ከጀመርን ከሶስት ቀናት ውስጥ ለውጥ ካላየን ተመልሰን የታከምንበት ጤና ማዕከል በመሄድ የህክምና ባለሙያ ማማከር ይገባናል።
- ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ የሆኑ ረግረግ ቦታዎችና ኩሬዎችን በአፈር በመሙላት፣ እንዲፈሱ በማድረግ በተጨማሪም በኩሬዎች ላይ የወባ ትንኝ እንዳትራባ ፀረዕጭ ኬሚካል መጨመር ይገባናል።




EPaRDA

ENHANCING PASTORALIST RESEARCH AND DEVELOPMENT ALTERNATIVES

TULLOW

EPaRDA 2013
Tel: 251-11-65-10-507
P.O.BOX: 30807 ADDIS ABABA, ETHIOPIA
eparda@ethionet.et